ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ወገኖች የጤናው ሴክተር ምላሽ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

2009 ዓ.ም

የተሳታፊ ማንዋል ⌖ ሞጁል አራት

# ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል



# ሞጁል 4፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል

**ማውጫ**

**መግቢያ ........ 2**

**4.1 የክፍለ ጊዜው አላማዎች ........ 2**

**4.2 ቅድሚያ መከላከል ተግባር ........ 2**

4.2.1 ቅድሚያ መከላከል ተግባር ምንድ ነው? ........ 2

4.2.2 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከል አስፈላጊነት ........ 5

4.2.3 ለዘላቂ የመከላከል ተግባር አስፈላጊ ሁኔታዎች ........ 6

**4.3 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን መከላከያ ስልቶችና የጤና ባለሙያዎች ሚና ........ 6**

4.3.1 በማህበረሰብ ደረጃ የሚከናወን የመከላከል ተግባር ........ 7

4.3.2 በተቋም ደረጃ የሚከናወን የመከላከል ተግባር ........ 12

**የሞጁል 4 ማጠቃለያ ........ 14**

**የተሳታፊዎች ግለ-ምዘና ........ 14**

## መግቢያ

በሞጁል 1 ስርዓተ-ፆታማለት ማህበረሰቡ የፈጠረውአመለካከት ሲሆንወንዶችና ሴቶች በማህበራዊ ግንኙነት ሂደት ውስጥ ያላቸውን ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች የሚወስን እንደሆነ አይተናል። በዚህ ሞጁል ውስጥይህንን ፅንሰሀሳብ ተከትለን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገጥቃት/በወሲባዊ ጥቃት ቅድመ መከላከል ተግባር አውድ ውስጥ የምንጠቀመው ሲሆንእነዚህ ጥቃቶች የሚከሰቱትም የማህበረሰብ አመለካከት በሚፈጥረው የሀይል አለመመጣጠን (ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ) ላይ ተመስርቶ ነው።የመከላከል ተግባሩ በባህሪይ ለውጥ መርሆች ላይ የሚያተኩር ሲሆንበወንዶች፣ በሴቶችና በህፃናት መካከል ያለውን ግንኙነት በአዎንታዊ መልኩ ለማጠናከር የማህበረሰብ መዋቅር የመጀመሪያ አሀድ ለሆነው ቤተሰብ ትኩረትያደርጋል።

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገጥቃት/ወሲባዊ ጥቃትጥቃቱ ከደረሰባቸውና ከተጎጂዎች በተጨማሪ በቤተሰቦች፣ በጓደኞችና በማህበረሰቦች ላይ ጉዳትና ዘለቄታዊ ተፅእኖዎችን ያሳርፋል። ስለዚህም ስርዓተ-ፆታንመሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከል ተግባር በጣም አስፈላጊ ግብ ነው።ወሲባዊ ጥቃት እንዲከሰት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ውስብስብ ሲሆኑ ሁሉንአቀፍና ውጤታማ የመከላከልተግባር ስልቶችን ማዘጋጀቱም ፈታኝነትአለው።

ይህም ሆኖስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገጥቃት በአለም ላይ የሰፊው ማህበረሰብ ጉዳይ ተደርጎ በመታየት ላይ ይገኛል።ስለዚህም የተለያዩ ተዋናዮች (መንግስታት፣ ለጋሾችና ሲቪል ማህበራት) ይህ አይነቱጥቃትእንዲቀጥል የሚያደርገውንውስብስብመንስኤ ለመፍታትተተገቢ የመከላከል ተግባርና ምላሽ መስጫ ስልቶችን ለመፍጠር በመስራት ላይ ናቸው።

### 4.1 የክፍለ ጊዜው አላማዎች

ይህ ክፍለ ጊዜ ሲጠናቀቅ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ይችላሉ ተብሎ ይጠበቃል፤

- የቅድመ መከላከል ተግባር ቁልፍ መርሆችን መግለፅ
- የማህበረሰብ ንቅናቄና የማህበራዊ ለውጥ ሂደትን ማብራራት
- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን በማህበረሰብና በጤና ተቋም ደረጃ በመከላከል ተግባር ረገድ የጤና ባለሙያዎች ያላቸውን ሚናዎች መግለፅ
- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎችን መለየት

**ቁልፍ ክህሎቶች፦**

***ግንዛቤ***

- የቅድሚያ መከላከል ተግባር ቁልፍ መርሆችን መግለፅ
- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን በመከላከል ተግባር ረገድ የጤና ባለሙያዎች ያላቸውን ሚናዎች መግለፅ

***ክህሎት***

- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎችን በንቃት መለየት
- በጤና ተቋማት ውስጥ የጤና ትምህርት ክፍለ ጊዜዎችን መምራት
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የማህበረሰብ ንቅናቄንና የማህበረሰብ ውይይትን እንዲመሩ መደገፍ መቻል

### 4.2 ቅድመ መከላከል ተግባር

#### 4.2.1 ቅድሚ መከላከል ተግባር ምንድነው?


ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል ማለትስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት እንዲከሰት የሚያደርጉ ሁኔታዎችን በማጥፋት ላይ ያነጣጠሩ የትኛውንም የተመረጡ ተግባራትን ማከናወን ነው።ይህም እጅጉን በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ የሚፈፀም አድልዎ እና በወንዶችና በሴቶች መካከል ካለው ተጨባጭ የእኩልነት መዛባት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገጥቃት/የወሲባዊ ጥቃት መሰረታዊ መንስኤዎችንመፍታት ያካተተ ነው።ከዚህም

ባለፈ ለጥቃት መከሰት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ማህበራዊ ልማዳዊ ደንቦችንና አካባቢያዊ ምክንያቶችን (ለምሳሌስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገጥቃትን/ለወሲባዊ ጥቃት ብዙም ቦታ የማይሰጡ አመለካከቶችና እምነቶች…) መፍትሄ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ሌላው እጅግ አስፈላጊ ነገር የመከላከል ስልቶቹ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የሚጋብዙ ሁኔታዎችን በመቀነስና መከላከያ ሁኔታዎችንም በማጠናከር ላይ ማተኮር አለባቸው፡፡ ይህ ደግሞ ጥቃቶችን ወይም የጥቃት ተጎጂነትን ከመነሻው የሚያስቀሩ የመከላከል ተግባራትን በማዘጋጀት ሊከናወን ይችላል፡፡

በተጨማሪም ሁሉንአቀፍ የመከላከል ተግባር ስልቶች በተለያዩ ደረጃዎች (ግለሰብ፣ ግንኙነት፣ ማህበረሰብ፣ እና ህብረተሰብ) ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ላይ ተፅእኖ የሚያሳርፉ ሁኔታዎችን በበቂ ደረጃ ማስተናገድ አለባቸው፡፡

__*ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ስነምህዳራዊ ማእቀፍ*__




Source: Heise 1998

ስነ-ምህዳራዊ ማእቀፍ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ላደረገ ጥቃት የሚያጋልጡ ምክንያቶችንና በተለያዩ ደረጃዎች (ግለሰብ፣ ግንኙነት፣ ማህበረሰብ እና ህብረተሰብ) ካሉ በርካታ ምክንያቶች ጋር ያላቸውን መስተጋብሮች ለመረዳት ሁሉን አቀፍ መሰረት ይሰጣል፡፡ ይህ የሆነው አንድ ነጠላ ምክንያት የተወሰኑ ሰዎች ወይም ቡድኖች ከሌላው በተለየ ለጥቃት ይበልጥ ተጋላጭ የመሆናቸውን እውነታ አሟልቶ ሊያስረዳ አይችልም ከሚል እውነታ ላይ ተመስርቶ ነው፡፡

ስለዚህም ይህ ሞዴል የመከላከልና ምላሽ የመስጠት ተግባራት ቀረፃ ወቅት ሊያገለግል ይችላል፡፡ የጤና ባለሙያዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን በተለይ ሴቶችንና ልጃገረዶችን ለጥቃት የሚያጋልጡ ምክንያቶችን እና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ለወሲባዊ ጥቃት መፈፀም አስተዋፅኦ የሚያበረክቱትን ምክንያቶችን ጭምር ለመረዳት ይህንን ሞዴል መጠቀም ይችላሉ፡፡ ይህ በተለያዩ ደረጃዎች ያሉትን አጋላጭ ምክንያቶች ለመቀነስ የትኞቹ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት መከላከያ ስልቶችና ተግባራት የበለጠ ውጤታማ መሆናቸውን ለመመዘን ይረዳቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት የመከላከል ተግባራት በግለሰብ የጤና ፍላጎቶች ላይ ብቻ የሚያነጣጥር ሳይሆን ለማህበራዊ ለውጥ አስፈላጊነትም ጭምር አጽንኦት የሚሰጡ ይሆናሉ፡፡

**በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ የሚገኙ የተለመዱ ለጥቃት የሚያጋልጡ ዋና ምክንያቶች በቀጣዩ ሰንጠረዥ ላይ ቀርበዋል፤**

| በስነምህዳራዊ ሞዴል መሰረት ለጥቃት የሚያጋልጡ ምክንያቶች | | | |
|---|---|---|---|
| **ግለሰብ**<br>*በግለሰቦች ባህሪያት ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ ግለሰባዊ ምክንያቶች* | **ግንኙነቶች**<br>*ከቤተሰብ፣ ከቅርብ አጋሮችና ከጓደኞች ጋር* | **ማህበረሰብ**<br>*ሰፈር፣ ት/ቤቶችና የስራ ቦታዎች* | **ህብረተሰብ**<br>*ጥቃት እንዳይገታ የሚያደርጉ ሰፊ ሁኔታዎች* |
| • ስርዓተ-ፆታ፣ እድሜ፣ ትምህርት<br>• የቤተሰብ የጥቃት ታሪክ<br>• ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ሲፈፀም መመልከት<br>• የህፃናት ጥቃት/ብዝበዛ ወይም የወላጅ ቸልተኛ አያያዝ ሰለባነት<br>• በቂ የሆነ የግል መተዳደሪያና ገቢ እጥረት<br>• ስራ አጥነት<br>• የአእምሮ ጤናና ባህሪያዊ ችግሮች<br>• አልኮልና አደገኛ ንጥረ ነገር አብዝቶ ተጠቃሚነት<br>• ሴተኛ አዳሪነት<br>• የአካል ጉዳተኝነት<br>• ከቀያቸው የተፈናቀሉ ስደተኞች | • የቤተሰብ መፍረስ<br>• ዘርን መሰረት ያደረገ የጥቃት ዝንባሌ<br>• ደካማ የህፃናት አስተዳደግ ተግባራት<br>• ጥቃት የተካተተበት የወላጆች ግጭት<br>• ጥቃት ከሚፈፅሙ ወይም ተገቢነት የጎደለው ባህሪይ ከሚያሳዩ ጓደኞች ጋር መወዳጀት<br>• ዝቅተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ<br>• ሴቶችን አለማብቃት<br>• ከሴቷ ጤናና ደህንነት ይልቅ ለቤተሰብ ክብር የበለጠ ቦታ መስጠት | • ከፍተኛ ስራ አጥነት<br>• ከፍተኛ የህዝብ ጥግግት<br>• የሴቶችና ቤተሰቦች ማህበራዊ መገለል<br>• የመረጃ እጥረት<br>• ለጥቃት ተጎጂ የሚደረግ በቂ እንክብካቤ አለመኖር<br>• ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን ጉዳያቸው ያላደረጉ ት/ቤቶችና የስራ ቦታዎች<br>• ስርዓተ-ፆታን መሰረት ላደረገ ጥቃት የማህበረሰቡ ቅጣቶች ደካማነት<br>• በህዝባዊ ስፍራዎች ያለው ደህንነት ደካማነት<br>• ልማዳዊ ስርአተፆታዊ ሚናዎችን መጋፋት<br>• የጥቃት ተጎጂን መውቀስ<br>• የጥቃት ተጎጂን ሚስጢር አለመጠበቅ | • ድህነት<br>• የኢኮኖሚያዊ፣ የማህበራዊና የስርዓተ-ፆታዊ እኩልነቶች መዛባት<br>• ደካማ ማህበራዊ ደህንነት/ደካማ ኢኮኖሚያዊ ሴፍቲ ኔት<br>• የወንድነት ገጽታ ከሀይለኛነትና የበላይነት ጋር መያያዝ<br>• የህግና የወንጀል ፍትህ ስርአት ደካማነት<br>• የጥቃት ፈፃሚዎች አለመከሰስ<br>• የጥቃት ተጎጂዎች ህጋዊ መብቶች አለመኖር<br>• የማህበራዊና የባህላዊ ልማዳዊ ደንቦች ጥቃትን መደገፍ |

**እነዚህን አጋላጭ ምክንያቶች በተመለከተ የጤናው ሴክተር ምን ሊሰራ ይችላል?**

| የጤናው ሴክተር በምን መልኩ መስራት እንዳለበት የሚያሳዩ ምሳሌዎች | |
|---|---|
| **ደረጃ** | **የጤናው ሴክተር ተግባራት** |
| **ግለሰብ** | • ለጥቃት የመጋለጥ እድል ያላቸውን ያገቡ ወጣት ሴቶች መለየት<br>• ከአልኮልና ከአደገኛ ንጥረነገርሱሰኛነት ሊያላቅቅ የሚችል አገልግሎቶችን መስጠት<br>• በክሊኒክና ማህበረሰብ አቀፍ ትምህርት መስጠት<br>• በኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የወጣቶች ስነተዋልዶ ጤና ፕሮግራሞች ውስጥ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን መከላከል |
| **ግንኙነት** | • ስርአተፆታ ፍትሀዊ ግንኙነቶችን ለማጎልበትና ልማዳዊ ደንቦችን፣ አመለካከቶችንና ባህሪያትን የመለወጥ አላማ ያላቸውን ፕሮግራሞች ለወንዶች ማዘጋጀት |
| **ማህበረሰብ** | • ለጥቃት ተጎጂዎች በሚቀርቡ አገልግሎቶች ላይ የማህበረሰቡን ድጋፍ ማጠናከር<br>• ማህበራዊ ጥምረቶችንና ትስስሮችን ማጠናከር |
| **ህብረተሰብ** | • የህክምና ህግ ስርዓት የሚቆጣጠሩ ህጎችና ፖሊሲዎች ማሻሻል (ለምሳሌ ከህግ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የህክምና ባለሞያዎች መጠቀም መጀመር)<br>• የህክምና ባለሙያዎች ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ከደረሰባቸው/ከተጎጂዎች ጋር በተገናኘ ያሉባቸውን ግዴታዎች የሚቆጣጠሩ ህጎችንና ፖሊሲዎችን ማሻሻል<br>• ሪፖርት ማድረግ አስገዳጅ እንዲሆን በህጎችና በፖሊሲዎች ማስቀመጥ<br>• ብሄራዊ የጤና ፖሊሲዎችና ፕሮቶኮሎች<br>• ፎረንሲክ ህክምናን የሚቆጣጠሩ ህጎች/ፖሊሲዎች |

**መልመጃ 4.1 በይቻላል ቀበሌ ውስጥ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል**

*ይሄንን መልመጃ እንዴት እንደምትሰሩት አመቻቹ ያሳዩዋችኋል። በቡድን ሆናችሁ የምትሰሩት ሲሆን ለማጠናቀቅም 30 ደቂቃዎች ይሰጣችኋል።*

**ምሳሌያዊ ታሪክ 1፡** እርስዎ ዋና የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ ሲሆኑ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን ከይቻላል ቀበሌ ማስወገድ ይፈልጋሉ። ይህንን ማድረግ እንደሚቻልም ተሰምቶዎታል። ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን እና እንዴት መከላከል እንደሚቻል የተመለከቱ ፅሁፎችን ማንበብም ጀምረዋል። ሊተገበሩ የሚችሉ የመፍትሄ ሀሳቦችን አግኝተዋል። ነገር ግን ያገኙት ስልታዊ መፍትሄ በቀበሌው ውስጥ ስላለው ሁኔታ ጥልቅ እውቀትና ግንዛቤ የሚጠይቅ ነው። እናም ሀሳብዎን ለቀበሌው አስተዳዳሪ ያወያዩትና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/የወሲባዊ ጥቃት መንስኤዎችን በተመለከተ ከጤና ልማት ሰራዊትና ከታወቁ የማህበረሰብ መሪዎች ጋር ስብሰባ ለማካሄድ ይወስናሉ። ከዚያም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቃሉ፤ .

1. በማህበረሰባችን ውስጥ ያለው ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት መሰረቱ ምንድን ነው/ናቸው?
2. ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ለወሲባዊ ጥቃት ቦታ የማይሰጡ በማህበረሰባችን ውስጥ የሚገኙ ማህበራዊ ልማዳዊ ደንቦች የትኞቹ ናቸው?
3. ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከል እነዚህን አሉታዊ ማህበራዊ ልማዳዊ ደንቦች እንዴት ነው መፍታት ያለብን?
4. ምን አይነት የመከላከል እርምጃዎችን መውሰድ ይገባናል? እንደግለሰብ፣ እንደቤተሰብ፣ እንደ ማህበረሰብና እንደ ህብረተሰብ?

### 4.2.2 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከል አስፈላጊነት

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በእጅጉ የተመሰረተው ጥቃቱ ሳይገታ እንዲቀጥል በሚያደርጉት በስርዓተ-ፆታዊ አድልዎ፣ በማህበራዊ ልማዳዊ ደንቦችና በስርዓተ-ፆታዊ ፍረጃ ላይ ነው። በተለይ በሴቶችና በህፃናት ላይ የሚፈፀመውን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት መጠንና ጥቃቱ በተጎጂዎቹ ላይ የሚያስከትላቸውን አሉታዊ ውጤቶች ከግንዛቤ ውስጥ ከገቡ ለጥቃት ተጎጂዎች ከሚደረገው ምላሽና አገልግሎት በተጨማሪ ጥቃቱን የመከላከልም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን መከላከልና ምላሽ መስጠት ስርዓተ-ፆታዊ እኩልነትን ለማረጋገጥ እና ሴቶችን ለማብቃት ቅድመ ሁኔታም ጭምር ነው። በእርግጥም ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ግለሰቦች በማህበረሰባቸው ውስጥ በሚገኙ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ደረጃዎች ሙሉ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ወይም አስተዋጽኦ እንዳያበረክቱ የሚያደርግ ትልቅ እንቅፋት ነው። ከዚህ በተጨማሪ እንዲህ አይነቱ ጥቃት የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ወይም ብዝበዛ ሲሆን (ለምሳሌ በሴቶች ላይ የሚደርስ ማንኛውም አይነት አድልዎን የማስወገድ ስምምነት/CEDAW ላይ እንደሰፈረው) ከበርካታ ጎጂ የጤና ለውጦች ጋር ስለሚያያዝም አደገኛ የማህበረሰብ የጤና ተግዳሮት ነው።

**<u>የቃላት ፍቺዎች</u>፡**

**አጠቃላይ መከላከል፡** አጋላጭ ምክንያቶችን ታሳቢ አድርገው በእነዚህ ምክንያቶች ላይ ያነጣጠሩ ስልታዊ የመከላከል እርምጃዎች የሚወሰዱበት ነው።

**ተፈላጊ መከላከል፡** "አጋላጭ ምክንያቶችን ታሳቢ አድርገው በእነዚህ ምክንያቶች ላይ ያነጣጠሩ ስልታዊ የመከላከል እርምጃዎች ሲሆኑ የቻሉትን ያህል "ገፍተው የሚሄዱ" ሁሉን አቀፍ አቀራረብ ያላቸው፣ በአሳታፊ መልኩ የሚተገበሩና ዲሞክራሲያዊ ባህሪይ ያላቸውና የታላሚ ቡድኑን ጤናና ደህንነት በማጠናከርና በማጎልበት ላይ ያተኮሩ ናቸው።"

**ሁለተኛ ደረጃ መከላከል፡** የክስተቱን መደጋገም ለማስወገድ የሚወሰዱ እርምጃዎች (ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎችን መለየትን ያካትታል)፡፡

**ሶስተኛ ደረጃ መከላከል፡** ክስተቱ ከደረሰ በኋላ ጥቃት ለደረሰባቸው ሰዎች የሚደረገውን እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም ለማሻሻልና ቋሚ የጤና ችግርን ለማስወገድ ቀደም ብሎ የሚካሄድ ተግባር ነው፡፡

### 4.2.3 ለዘላቂ የመከላከል ተግባራት አስፈላጊ ሁኔታዎች

*ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን በዘላቂነት የመከላከል ተግባራት የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፡*

- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/የወሲባዊ ጥቃት ችግር ፋትና ተፅእኖ በተመለከተ ግንዛቤን ማሳደግ
- በወንዶችና በሴቶች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች የሚወስኑ ስርዓተ-ፆታዊ እሴቶችን፣ ልማዳዊ ደንቦችንና አንፃራዊ የስልጣን የሀይል ሚዛንን መከላከል
- ሰዎችን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ላደረገ ጥቃት/ለወሲባዊ ጥቃት ይበልጥ ተጋላጭ የሚያደርጉ አጋላጭ ሁኔታዎችን መለየትና ለማስወገድ መሞከር
- ስጋት ቀናሽ ዘዴዎችንማካተት (በጥቃት ፈፃሚ ላይ ያተኮሩ)፤ ይኸውም የአንድን ግለሰብ ጥቃት የመፈፀም እድል ለመቀነስ ሲባል አጋላጭና ተከላካይ ሁኔታዎችንለመቀየርየሚጥሩስልቶችን ማካተት፡፡
- ወሲብን የተመለከተ የፈቃደኝነት ስምምነት ይዘቶች ላይ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ
- ስለወሲባዊ ጥቃትና ስለትንኮሳ እውቀትና ግንዛቤን ማሳደግ
- በመከባበር ላይ የተመሰረተ ግንኙነትንና ስርዓተ-ፆታዊ እኩልነትን ለማጎልበት ታዳጊ ህፃናትንና ልጃገረዶችን ማስተማርና ከእነሱ ጋር አብሮ በመስራት በለጋ የህይወት እድሜ ላይ መጀመር
- ሴቶችን የሚያበቁ፣ በኢኮኖሚ ራስን የሚያስችሉና ደህንነታቸውን የሚያሻሽሉ ተግባራትን ማካተት
- በቤት ውስጥ እንዲሁም በማህበራዊና በፖለቲካዊ መስኮች የሴቶችን ተሳትፎና የውሳኔ-ሰጪነት አቅም በማሳደግ ላይ ማነጣጠር
- የመከላከልና ክለላ የመስጠት ተግባር ለማከናወንና መልእክቶችን ለማሰራጨት በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ማነጣጠር (በግለሰብ፣ በግንኙነት፣ በማህበረሰብ፣ በህብረተሰብ)
- የወሲባዊና ስነ-ተዋልዷዊ ጤና ርእሰ-ጉዳዮችን በተመለከተ ግንዛቤን ማሳደግ
- ጥቃት ሲከሰት የሚመለከቱ ሰዎችን አዎንታዊ ባህሪያት ማሳደግ
- መደበኛና እርስ በእርስ የሚመጋገቡ መልእክቶችን በቋሚነት ለማህበረሰቡ ማቅረብ፡፡ ይሄ የማህበረሰቡን አመለካከት ለመለወጥና የለውጥ ግስጋሴውን ለማገዝ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡
- (ሰብአዊ) መብት-ተኮር አቀራረብን መከተል (የመቻቻል ባህልንና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ከወሲባዊ ጥቃት ፈፃሚዎች ጋር በተያያዘ ያለውን ከቅጣት የማምለጥ ሁኔታ ማስቀረት)
- የጤና ባለሙያዎች ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ለወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች በቂ እንክብካቤ መስጠት የሚያስችላቸው እውቀት፣ አመለካከትና የተግባር ክህሎት እንዲኖራቸው ማድረግ እና ጤና ባለሙያዎችን ስለተለያዩ የሪፈራል እድሎች በቂ መረጃ ማስጨበጥ፡፡

## 4.3 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን መከላከያ ስልቶችና የጤና ባለሙያዎች ሚና

- ❖ **የሰብአዊ መብት አቀራረብ**

በሞጁል 1 ውስጥ እንዳየነው አለም አቀፋዊና ክፍለ አህጉራዊ የሰብአዊ መብት እስታንዳርዶች ሀገራዊ ተፈፃሚነትን ይጠይቃሉ፡፡ ይህ ማለት ተፈራራሚ መንግስታት ህጋዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ፖሊሲ ነክ ወይም ፕሮግራም ነክ አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ የሚጠበቅባቸው ሲሆን ለተፈፀሙ ጥቃቶችም

ተገቢውን ህጋዊ ቅጣት በመስጠት ዜጎች መብታቸውንና ነፃነታቸውን እንዲያጣጥሙ ማድረግ አለባቸው፡፡

በተመሳሳይ መልኩም ሰብአዊ መብቶች መብትን ብቻ ሳይሆን ግዴታም የሚጭኑ ሲሆን መንግስት ደግሞ ዋነኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ በዚህም መሰረት ተፈራራሚ መንግስታት በአለም አቀፍ ህግ መሰረት የሁሉንም ግለሰቦች ሰብአዊ መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታና ሀላፊነት ያለባቸው ሲሆን የሰብአዊ መብቶችን በተጨባጭ መከበር የሚጥሱ ወይም የማይደግፉ ተግባራት የሰብአዊ መብቶችን ግዴታዎች ይፃረራሉ፡፡

እናም መብት-ተኮር አቀራረብ ሰብአዊ መብቶችን በከፍተኛ ደረጃ ማጣጣም የሚያስችል አካባቢ መፈጠርን ታሳቢ ያደርጋል፡፡

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትና ወሲባዊ ጥቃት የተጠቂው ሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ሲሆኑ እነዚህን ጥቃቶች ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ በቂ እርምጃዎች በሙሉ መወሰድ አለባቸው፡፡

*የኢትዮጵያ መንግስት ያለበትን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ወገኖች ሰብአዊ መብቶች የማስከበር፣ የማስጠበቅና የማሟላት ግዴታን በተመለከተ የጤና ባለሙያዎች የድልድይነት ወይም የመንግስትን ሀላፊነት የሚወጡ ተዋናዮች ሆነው ያገለግላሉ፡፡*

### ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን በመከላከል ሂደቶች በሙሉ የጤና ባለሙያዎች ሚና አስፈላጊነት፡-

በአለም አቀፍ የጤና ድርጅት (WHO) መሰረት ወሲባዊ ጥቃት የማህበረሰብ ጤና ችግር ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት የጤናው ሴክተር ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን በመከላከል ረገድ የመሪነት ሚና መጫወት ይገባዋል፡፡ በእርግጥም የጤና ባለሙያዎች የተመደቡበት ቦታ እንደነዚህ አይነት ጥቃት የደረሰባቸውን ሰዎች ለመለየትና ለማስተናገድ በእጅጉ የተመቸ ነው፡፡ ለጥቃት ተጎጂዎች ረዘም ላለ ጊዜ በተደጋጋሚ እንክብካቤ የሚያደርጉ ሲሆን እግረመንገዳቸውንም ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የሚያስከትላቸውን በርካታ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ተጽእኖዎችን ይገነዘባሉ፡፡ ከዚህ በላይ በሞጁል 2 ውስጥ እንደተጠቀሰው ዘርፈብዙዊ አቀራረብ ይበልጥ የተቀናጀና የተዋቀረ ትብብር ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር (ሪፈራል ኔትወርክ) እንዲኖር የሚያመቻችና የጤና ባለሙያዎች ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ለወሲባዊ ጥቃት አቅማቸው የሚፈቅደውን ከፍተኛ እንክብካቤ እንዲሰጡ እድል ይሰጣል፡፡ ሩህሩህነት የተሞላበት፣ ከፍረጃ የፀዳና ሁሉን አቀፍ እንክብካቤ ለሁለተኛና ለሶስተኛ ደረጃ የመከላከል ተግባር አስተዋፅኦ አለው፡፡

*በማህበረሰብና በጤና ተቋማት ደረጃ ለሚካሄድ የመከላከል ተግባር ሁለት ዋነኛ እስትራቴጂዎች አሉ፡፡*

## 4.3.1 በማህበረሰብ ደረጃ የሚከናወን የመከላከል ተግባር

### ሀ. የማህበረሰብ ንቅናቄና የማህበራዊ ለውጥ ሂደት

በማህበረሰብ ውስጥ በጤና ኤክስቴንሽኖች አማካኝነት የሚካሄደው ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/የወሲባዊ ጥቃት ቅድመ መከላከል ተግባር ወሳኝና በእጅጉ አስፈላጊ ተግባር ነው፡፡

**የመከላከልና የማነሳሳት ፕሮግራሞች** በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ አዎንታዊ የባህሪይ ለውጥን ለማጎልበትና በሂደትም ይህ አይነቱን ጥቃት ለማጥፋት በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ የማህበረሰብን ልማዳዊ ደንቦች መቀየር ሂደት እንጂ የአንድ አጋጣሚ ክስተት አይደለም፡፡ ሰዎች በተፈጥሯቸው በለውጥ ሂደት ውስጥ በሚያልፉበት አካሄድ ግንዛቤ ላይ የተመሰረቱ ተግባራት በዘፈቀደ ወደ ማህበረሰቡ ከሚረጩ መልእክቶች የበለጠ ውጤታማ ናቸው፡፡

ሰዎች የቤት ውስጥ ጥቃት ችግርን እንዲለዩ፣ ተፅእኖውን እንዲያስተውሉ፣ የራሳቸውን ባህሪያት እንዲገመግሙና ከዚያም በህይወታቸው ውስጥ ለውጦችን ማካሄድ እንዲጀምሩ የሚጠይቅ ነው፡፡ ምንም

እንኳን እያንዳንዱ ግለሰብ ልዩና የቤት ውስጥ ጥቃትን በተለያየ መልኩ የሚመለከት ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜ ግለሰቦች የሚያልፉበት የለውጥ ሂደት ግን ተመሳሳይ አካሄድ የሚከተል ነው፡፡

ግለሰቦች ባህሪያቸውን እንዴት መለወጥ እንደሚችሉ የሚያስረዳው የለውጥ ደረጃዎች ፅንሰሀሳብ የማህበረሰብ ንቅናቄ ስልቶችን ለመንደፍ ሊያገለግል ይችላል፡፡

| የግለሰብ ለውጥ ደረጃዎች | የማህበረሰብ ንቅናቄ ምእራፎች |
|---|---|
| **ደረጃ 1፡ ቅድመ-ማሰላሰል፡** ግለሰቡ ጉዳዩን/ችግሩን እና በህይወቱ/ቷ ላይ ያለውን ተጽእኖ አላስተዋለም/ችም፡፡ | **ምእራፍ 1፡ የማህበረሰብ ግምገማ፡** የቤት ውስጥ ጥቃትን በተመለከተ ስላሉት አመለካከቶችና እምነቶች መረጃ መሰብሰብና ከማህበረሰብ አባላትና ከሙያ ሴክተሮች ጋር ግንኙነት መገንባት መጀመር |
| **ደረጃ 2፡ ማሰላሰል፡** ግለሰቡ/ቧ ጉዳዩ/ችግሩ ከህይወቱ/ቷ ጋር ስላለው/ላትግንኙነትማሰላሰልይጀምራል/ትጀምራለች | **ምእራፍ 2፡ ግንዛቤ መፍጠር፡** በቤት ውስጥ ጥቃት የተለያዩ ገፅታዎች፣ የሚከሰትባቸውን ምክንያቶች እና በሴቶች፣ በወንዶች፣ በቤተሰቦችና በማህበረሰብ ላይ የሚያስከትላቸውን አሉታዊ ተፅእኖዎች በተመለከተ ግንዛቤ መፍጠር ይቻላል |
| **ደረጃ 3፡ ለእርምጃ መዘጋጀት፡** ግለሰቡ/ቧ የበለጠ መረጃ ያገኝና/ታገኝና ለተግባር ይነሳሳል/ትነሳሳለች፡፡ | **ምእራፍ 3፡ ትስስሮችን መገንባት፡** የቤት ውስጥ ጥቃትን ለመከላከልና የሴቷን/የወንዱን የደህንነት መብት ለማስከበር በግለሰብና በቡድን ደረጃ የሚደረጉትን ጥረቶች ለማጠናከር የማህበረሰብ አባላት ሊሰባሰቡ ይችላሉ |
| **ደረጃ 4፡ እርምጃ፡** ግለሰቡ/ቧ አዲስና የተለየ የአስተሳሰብና የባህሪይ አማራጮችን መሞከር ይጀምራል/ትጀምራለች፡፡ | **ምእራፍ 4፡ የማካተት እርምጃ፡** አሁን የቤት ውስጥ ጥቃትን የመከላከል ተግባር የማህበረሰብ የእለት ተእለት ኑሮና የተቋማት ፖሊሲዎችና አሰራሮች አካል ማድረጊያ ጊዜ ነው |
| **ደረጃ 5፡ ማስቀጠል፡** ግለሰቡ/ቧ የባህሪይ ለውጡን ጠቀሜታዎች ይገነዘባል/ትገነዘባለች፤ በዛው ባህሪይም ይቀጥላል/ትቀጥላለች | **ምእራፍ 5፡ ውጤቶችን ማጠናከር፡** አሁን የቤት ውስጥ ጥቃትን የመከላከል ስራውን ዘለቄታዊነት፣ የእድገቱን መቀጠልና መሻሻል ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እርምጃዎችንና ተግባራትና ማጠናከሪያ ጊዜ ነው |

**መልመጃ 4.2 በይቻላል ቀበሌ ውስጥ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል (የቀጠለ)**

*ይሄንን መልመጃ እንዴት እንደምትሰሩት አመቻቹ ያሳዩዋችኋል፡፡ በቡድን ሆናችሁ የምትሰሩት ሲሆን ለማጠናቀቅም 30 ደቂቃዎች ይሰጣችኋል፡፡*

**ምሳሌያዊ ታሪክ፡** ኢላማዎን/ግብዎን ስልታዊ በሆነ መንገድ ማሳካት የሚያስችልዎትን መረጃ በሙሉ ከቀበሌዎ አሰባስበዋል፡፡ የማህበረሰቡን ባህሪይ ለመለወጥ ከባልደረባዎ ጋር በመሆን የማህበረሰብ ንቅናቄ እስትራቴጂ ለመንደፍ ሞክራችኋል፡፡

*በዚህ የነደፋችሁት እስትራቴጂ ውስጥ መካተት የሚገባቸው ነገሮች ምንድናቸው? ወይም በእያንዳንዱ የማህበረሰብ የባህሪይ ለውጥ ደረጃዎች የትኞቹ መርሆች ይስተናገዳሉ?*

***እያንዳንዱን የለውጥ ደረጃ ለማስተናገድ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችና የጤና ባለሙያዎች የሚከተሉትን መፈፀም አለባቸው፡***

- **መብት-ተኮር አቀራረብን ስራ ላይ ማዋል**

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የሰብአዊ መብቶች ጥሰት በመሆኑ ይህ አይነቱን ጥቃት በመከላከል ረገድ የጤና ባለሙያዎች መብት-ተኮር አቀራረብን በስራ ላይ ማዋል አለባቸው፡፡በእርግጥም ሰብአዊ መብቶች ሁሉን አቀፍ እንደመሆናቸውከስርዓተ-ፆታና ከስርዓተ-ፆታ እኩልነት ጋር አያይዘን የሰብአዊ መብት ጉዳዮችን ማንሳትና በመከላከል እስትራቴጂዎቻችንና ፕሮግራሞቻችን ውስጥ የግለሰቦችን ሰብአዊ መብቶች ማጉላት አስፈላጊ ነው፡፡

- **የግንዛቤ መፍጠሪያ ተግባራትን ማደራጀትና ማጠናከር**

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን ለመከላከል የስርዓተ-ፆታ እኩልነትን የማሳደግና ልማዳዊ ደንቦችን የመቀየር ጥረቶች ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡በሂደትም የጤና ባለሙያዎች የቤት ለቤት ጉብኝት በማካሄድ፣ የጤና ልማት ሰራዊት ስብሰባዎችን በማዘጋጀትና ሌሎች መድረኮችን ወይም የህዝብ መሰብሰቢያ አጋጣሚዎችን በመጠቀም የሁሉንም የማህበረሰብ አባላት (ሴቶች፣ ወንዶች፣ ታዳጊ ወንዶችና ልጃገረዶች) ግንዛቤ ማሳደግ አለባቸው፡፡እንደነዚህ አይነት ስራዎች የህዝቡን አመለካከቶች ለመፈተሽና እውቀታቸውን ለማሳደግ የሚያግዙና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን ተቀባይነት (ሚስት መደብደብ) በተመለከተ ያሉትን አመለካከቶች፣ ባህሎችና የማህበረሰብ ልማዳዊ ደንቦች ለመለወጥ ከፍተኛ አቅም ያላቸው ሲሆን ጥቃት የቤተሰብ የውስጥ ጉዳይ ነው የሚለውን አፈታሪክ ለማስወገድም ያስችላሉ፡፡

- **የወንዶችን ተሳትፎ ማሳደግ**

የጤና ባለሙያዎች በማህበረሰቡ ውስጥ የወንድ ቡድኖችን በማደራጀት ስለወንዶች ማህበራዊ ተሳትፎና ስርዓተ-ፆታ ሚናዎች እንዲነጋገሩና ከሴቶች ጋር ባላቸው ግንኙነት ውስጥ ስላላቸው ተፅእኖዎች እንዲወያዩ ማድረግ፡፡
ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን በመከላከል ሂደት ውስጥ አስተዋፅኦ ለማድረግ አባዊነት፣ የወንድ የበላይነትና የልዩ መብት ተጠቃሚነት መኖሩን በተመለከተ በአስተውሎት መመርመር ለወንዶች አስፈላጊ ነው፡፡

ከዚህም በላይ ምንም እንኳን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት በሴቶችና በልጃገረዶች/በህፃናት ላይ በከፍተኛ ደረጃ መከሰቱና ወንዶች ደግሞ ዋነኛ የጥቃቱ ፈፃሚዎች የመሆናቸው እውነታ እየቀጠለ ቢገኝም ስርዓተ-ፆታና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት "የሴቶች ጉዳይ" አለመሆኑና አዋቂና ወጣት ወንዶችም የጥቃቱ ተጎጂ ሊሆኑ እንደሚችሉ መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት አለምአቀፋዊና የሰፊው ማህበረሰብ ጉዳይ ነው፡፡

- **ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን ቋሚ አጀንዳ ማድረግ**

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን ቋሚ አጀንዳ ለማድረግ የማህበረሰብ ውይይቶችን በማመቻቸትና በማከናወን የጤና ሰራተኞች ማህበረሰቡ ወሳኝ ጽንሰ-ሀሳቦችንና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት መንስኤዎችንና የሚያስከትላቸውን ተፅእኖዎች በተመለከተ ያለውን እውቀትና ግንዛቤ ማሻሻል ይችላሉ፡፡ ከዚህ ባለፈ እነዚህ ተግባራት ይህ አይነቱ ጥቃት ስላለው አደገኛነት አፅንኦት ለመስጠትና በማህበረሰቡ ላይ የሚያስከትሏቸውን አሉታዊ ተፅእኖዎች ለማሳየት ያስችላሉ፡፡

- **ቅድሚያና ሁለተኛ ደረጃ መከላከልን ማጠናከር**

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን በመከላከል ሂደት ውስጥ መብታቸውን እሚያስጠብቅና አገልግሎቶችን ተደራሽ ያደረገ (ጤና ነክ እና ሌሎች ማህበራዊና ህጋዊ አገልግሎቶችን) በቂ ምላሽ ለጥቃቱ ተጎጂዎች መስጠት ወሳኝ ነው፡፡ ስለዚህም የጤና ባለሙያዎች በአገልግሎት ሰጪ ተቋማትና በሰፊው ማህበረሰብ መካከል ያለውን ትብብር ማጠናከር አለባቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለጥቃት ተጎጂዎች የአገልግሎቶችን ተደራሽነት ለማሻሻል የሚደረጉ ጥረቶችን መደገፍ የሚገባቸው ሲሆን ይኸውም፡-

- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸውን በንቃት መለየት፤
  - የቤት ለቤት ጉብኝትን ምቹ አጋጣሚን በመጠቀም ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገጥቃት/ከወሲባዊ ጥቃት ጋር የተገናኙ ርዕስጉዳዮችን በቤተሰብ ትምህርትና በሚሰጧቸው መከላከልተኮር መልእክቶች ውስጥ ማካተት
  - ቤተሰቦች ስለተከሰቱስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች/ወሲባዊ ጥቃቶች ግልፀኝነት እንዲኖራቸው ማገዝና ለጥቃት ተጎጂዎች የተመቻቹ አገልግሎቶችንና የድጋፍ እንክብካቤዎችን የተመለከተ መረጃ መስጠት
  - ቤተሰቦች ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ርእስጉዳይን ጨምሮ ስለጤነኛ የቤተሰብ ግንኙነቶች መደበኛ ውይይት የሚያካሂዱባቸውን መድረኮች/ፎረሞች እንዲያቋቁሙ ቤተሰቦችን ማገዝ
  - ጥቃቶች ሲፈፀሙ ሪፖርት የሚያደርጉባቸውንና አገልግሎት የሚያገኙባቸውን መንገዶች ለቤተሰቦች ማሳወቅ

ጤና ተቋም የመጣ ታካሚ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ደርሶበት ሊሆን እንደሚችል ጥርጣሬ በሚኖርበት ወቅት ማድረግ ስለሚገቡን ነገሮች የተመለከቱ መረጃዎችን ከፈለጉ ቀጣዩን ክፍል ይመልከቱ፡፡

**መልመጃ 4.3 የቡድን ጥያቄዎችና መልሶች**

*አመቻቹ ለሁለት ቡድኖች ይከፍሏችሁና ለእያንዳንዱ ቡድንም ጥያቄዎችን ያቀርባሉ፡፡ አመቻቹ ለሚያቀርቡት ጥያቄ መልስ የሚሰጠውን የቡድን አባል የሚመርጥ የቡድን አለቃ እያንዳንዱ ቡድን ይሾማል፡፡ መልመጃውን ትኩረት ሰጥታችሁ ተከታተሉ፤ የተወሰነ ግብረገብነትና በአጭር ጊዜ ውስጥ (በሰኮንዶች) መልስ መስጠትን ይጠይቃል፡፡*

*ይህን ተግባር ለመጭረስ 20 ደቂቃ ካባቢ ሊፈጅ ይችላል፡፡*

*ይህንን መልመጃ ለማጠናቀቅ በግምት 20 ደቂቃዎች ይወስዳል፡፡*

**ለ) ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት በተጎጂዎች/ጥቃት በደረሰባቸው ሰዎች ቤተሰቦችና በማህበረሰቡ ላይ የሚያስከትለውን ተፅእኖ ማስተናገድ**

በሞጁል 1 ውስጥ እንደተመለከትነው ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት መጠን ከቀላል እስከ ከባድ አካላዊ ጉዳት እና ከስነ-ልቦናዊ ችግሮች እስከ ሞት ሊደርስ ይችላል፡፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የሚያስከትላቸውን ከባድ ተፅእኖዎች በተመለከተ ለጥቃቱ ተጎጂ/ጥቃቱ ለደረሰባቸው ሰዎች የቅርብ በሆኑ ሰዎች ለምሳሌ በቤተሰብ አባላት ላይ የሚደርሱ ተፅእኖዎችን ማስተናገድ ጠቃሚ ነው፡፡ ከዚህ በላይ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት በተጎጂዋ/ጥቃቱ በደረሰባት ግለሰብ ማህበረሰብ ላይ የሚያስከትለው ተፅእኖ ቦታ ሊሰጠውና በዛው ልክም ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡ እነዚህ ተፅእኖዎች ቅፅበታዊ፣ አጭር ጊዜ የሚቆዩ እና ከወላጅ ወደ ልጆች የሚተላለፉ ሊሆኑ ስለሚችሉ በመከላከል ስልት ውስጥ መስተናገድ አለባቸው፡፡

- **ቤተሰብ ላይ የሚደርሱ ተፅእኖዎች**

- ፍቺ/የቤተሰብ መፍረስ፤ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊጥቃት በደረሰ ማግስት የትዳር አጋር ወይም የፍቅርጓደኛየሆነው/ችው ሰው የጥቃት ተጎጅን ሊተው/ዋት ይችላል/ትችላለች፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ ከእንደዚህ አይነት ጥቃቶች ጋር ተያያዥነትባለው ሀፍረትና መገለል የተነሳ ነው፡፡ ስለዚህም መገለልን ለማስወገድና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊጥቃት የሚያስከትለውን አሉታዊ የአመለካከት ተፅእኖ ለመቀነስ ግንዛቤ የማሳደግና የማነሳሳትፕሮግራሞች በእጅጉ አስፈላጊ ናቸው፡፡
- የቤተሰብ ኢኮኖሚያዊና ስነልቦናዊ እድገት አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡
- እናትየዋ ጥቃት የተፈፀመባት በእርግዝናዋ ወቅት ላይ እያለች ከነበረ በዚሁ ምክንያት ህፃኑ የጤና ችግሮችን ይዞ ሊወለድ ይችላል፡፡
- ጥቃት በሚፈፀምበት ቤተሰብ ውስጥ የሚያድጉ ህፃናት የጥቃት ተጋላጭነት እድልን ይጨምራል፡፡
- በቤታቸው ውስጥ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ሲፈፀመ የተመለከቱ ህፃናት የተለያዩ አደገኛ ተፅእኖዎች ይደርሱባቸዋል፤ ለምሳሌ ራስን ማግለል፣ ዝቅተኛ ግለ-ግምት፣ ቅዠቶች፣ ራስን መውቀስ፣ እኩዮችንና የቤተሰብ አባላትን ማጥቃት፣ ንብረት ማውደም፤ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ፈፃሚ የመሆን ወይም የጥቃቱ ተጎጂ የመሆን እድል መስፋት፡፡
- የጥቃት ተጎጅዎች ለልጆቻቸው የሚያደርጉት እንክብካቤ ሊዳከም ይችላል፡፡
- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/የወሲባዊጥቃትተጎጂ በእነዚህ አይነት ጥቃቶች አጋጣሚ የተፀነሰውን/ችውን ልጅ/ት አልቀበልም ልትል ወይም አሉታዊ አመለካከት ልትይዝበት ትችላለች፡፡

**ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ተጎጂዎች ቤተሰቦች የሚደረጉ ስነ-ልቦናዊ-ማህበራዊ ድጋፎች**

- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በጥቃቱ ተጎጂዎች ደህንነት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የማስከትል እድሉ ሰፊ በመሆኑ ለቤተሰብ አባላት ስነ-ልቦናዊ-ማህበራዊ ድጋፎችን ማዘጋጀት ተገቢነት አለው፡፡ ይህ አይነቱ የድጋፍ ተግባር በቤተሰብ ላይ የሚደርሰውን አጠቃላይ ጎጂ ተፅእኖ ለመቀነስና በተመሳሳይ ጊዜም ሰፊውን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/የወሲባዊ ጥቃት ርእሰ ጉዳይ ተደራሽ ለማድረግ ያግዛል፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች እንደዚህ አይነት በጥቃት የተጎዱ ቤተሰቦች ሲያጋጥሟቸው ከጤና ባለሙያዎች ወይም የስነ-ልቦና ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ ማግኘት አስፈላጊ መሆኑን ማሳወቅ አለባቸው፡፡

- **በማህበረሰብ ላይ የሚደርሱ ተፅእኖዎች**

- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት በጤና እና በፍትህ ስርአት ላይ ጫና ሊፈጥር ይችላል
- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎች ለምርታማነት አስተዋፅኦ ላያደርጉ ስለሚችሉ በኢኮኖሚ እድገትና መረጋጋት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊደርስ ይችላል
- ለሴቶች የልማት ተሳትፎ እንቅፋት ሊሆንና ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ያላቸውን አስተዋፅኦ ሊቀንስ ይችላል
- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ያለውን መተማመን ያፈርሳል
- የሰዎች የኑሮ ስልት/ዘይቤ መሰረት ያደረጉባቸው የመደጋገፊያ ቁርኝቶች መዳከም
- ውጥረትና ብጥብጥ በሚከስትባቸው ወቅቶች የማህበረሰቡን አቅም ለማጠናከር በእጅጉ አስፈላጊነት ያላቸው ቁርኝቶች መሳሳትና መበታተን

በማህበረሰብ ላይ የሚደርሱ ተፅእኖዎች እነዚህ ብቻ አይደሉም፡፡ስለዚህም ማህበራዊ ድጋፍ አድሏዊ ያልሆኑ አቀራረቦችን በማጠናከር፣ በማህበረሰብ ጥረቶች ውስጥ የጥቃት ተጎጂዎችን ተቀብሎ በማሳተፍና የማህበረሰቡ አባልነት ስሜት እንዲሰማቸው በማድረግ እንዲሁም ደጋፊ አካባቢን በመፍጠር የጥቃት ተጎጂ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦቻቸውና ሰፊው ማህበረሰብ ከደረሰባቸው ጉዳቶች በፍጥነት እንዲያገግሙ ያደርጋል፡፡

### 4.3.2 በተቋም ደረጃ የሚከናወን የመከላከል ተግባር

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ወገኖች በጤና ተቋማት ውስጥ በጤና ባለሙያዎች የሚስተናገዱበት መንገድ እንዲሁም ለተጎጅዎች ማህበራዊና ህጋዊ ድጋፎችን ከሚያካትተው ዘርፈብዢዊ አቀራረብ አንጻር እንደዚህ አይነት ጥቃቶችን በማስወገድ አላማ ውስጥ ወሳኝ ሚና አለው፡፡
በእርግጥም ርህራሄ የተሞላበትና ተገቢነት ያለው እንክብካቤ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣል፡፡ ይህም ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት መንስኤዎችንና የሚያስከትላቸውን ተፅእኖዎች ለመለየትና ይበልጥ ለመረዳት እንዲሁም አጋላጭ ሁኔታዎችን ለማስወገድና ከጥቃት የሚከላከሉ ሁኔታዎችን ለማጠናከር አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ከጤና አገልግሎቶች ተደራሽነት አንፃር የስርዓተ-ፆታ እኩልነት እንዲጠናከር አስተዋፅኦ ማበርከትና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊጥቃት ተጎጂዎች ከአካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳታቸው በፍጥነት ማገገም ይችሉ ዘንድ ሊጠቀሟቸው ስለሚችሏቸው የተለያዩ (ስፔሻላይዝድ) አገልግሎቶች ትክክለኛ መረጃ መስጠት መቻል አለባቸው፡፡

- ***ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የተጋለጡ የጥቃት ተጎጂዎችን መለየት***

የጤና ችግሮች በጥቃት ምክንያት ሊከሰቱ ወይም ሊባባሱ እንደሚችሉ የጤና ባለሙያዎች መገንዘብ አለባቸው፡፡
የጥቃት ተጎጂ የሆኑና በተለይም ከቅርብ ሰው ጋር ባላቸው ግንኙነት ውስጥ ጥቃት የተፈፀመባቸው ሴቶችና ህፃናት አብዛኛውን ጊዜ ለሚከሰትባቸው ስሜታዊና አካላዊ ጉዳቶች የህክምና አገልግሎት ይፈልጋሉ፡፡ ነገር ግን ከሀፍረትና ከጥፋተኝነት ስሜት በመነጨ ወይም የሰዎችን ፍረጃ በመፍራት ጥቃቱን ሁሌ ይፋ አያደርጉም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሚስጢር አለመጠበቅና የአፀፋ እርምጃ ስጋት የጥቃት ተጎጂዎች ዝምታን እንዲመርጡ ሊያደርጓቸው ይችላሉ፡፡
ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊጥቃት ተጎጂዎችን በቶሎ መለየት በቂ እንክብካቤ ለመስጠትና ክትትል ለማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህም የጤና ባለሙያዎች ታካሚዎችን በሚመረምሩበትና በሚያክሙበት ወቅት ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊጥቃት ተከስቶ ሊሆን እንደሚችል ማስተዋል አለባቸው፡፡

*በአንዲት ሴት ላይ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ሲያስተውሉ ይጠርጥሩ፡-*

- *ቀጣይነት ያላቸው ስሜታዊ የጤና ችግሮች ለምሳሌ ውጥረት፣ ጭንቀት ወይም ድባቴ*
- *ጎጂ ባህሪያት ለምሳሌ አልኮል ወይም አደገኛ ንጥረነገር ተጠቃሚነት*
- *ራስን ለመጉዳት ወይም ራስን ለማጥፋት ሀሳቦች፣ እቅዶች ወይም ድርጊቶች (ሙከራዎች)*
- *ተደጋጋሚ የአካላዊ ጉዳቶች ወይም ምንጫቸውን ለመግለፅ የሚያስቸግሩ አካላዊ ጉዳቶች*
- *ተደጋጋሚ የአባለዘር ኢንፌክሽኖች*
- *ያልታቀደ/ያልተፈለገ እርግዝና*
- *ምንጫቸውን ለመግለፅ የሚያስቸግር ስር የሰደዱ ህመሞች ወይም ሁኔታዎች (የዳሌ ህመም ወይም ወሲባዊ ችግሮች ወይም የሽንት ፊኛ ችግሮች፣ የጨጓራና አንጀት ችግሮች፣ የኩላሊት ወይም የሽንት ፊኛ ኢንፌክሽን፣ ራስ ምታት)*
- *ምንም አይነት ግልፅ የጤና ምርመራ ውጤት በሌለበት ተደጋጋሚ የጤና ምክክር ማካሄድ*

የአንዲት ሴት አጋር ወይም ባል በምክክር ወቅት ጣልቃ የሚገባ ከሆነ፤ የራሷን ወይም የልጆቿን የህክምና ቀጠሮ ብዙ ጊዜ የምታሳልፍ ከሆነች፤ ወይም ልጆቿ ስሜታዊና ባህሪያዊ ችግሮች ካለባቸው ጥርጣሬ ሊሰማዎት ይገባል፡፡

የጤና አገልግሎት ፈልገው የመጡ ሴቶችን ሁሉ መመርመር አይመከርም፡፡ ይህም ሆኖ የጤና ባለሙያዎች ከአደጋ ጋር የማይያያዙ ወይም በአደጋ ምክንያት እንዳልተከሰቱ የሚጠረጥሯቸውን አካላዊ ጉዳቶች ወይም የጤና ሁኔታዎች በሚያስተውሉበት ጊዜ ለሴት ታካሚዎች ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ስለወሲባዊ ጥቃት አንስተው እንዲወያዩ ይበረታታል፡፡

***ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት መፈፀሙን ከተጠራጠሩ፡-***

- አንዲት ሴት ብቻዋን ካልሆነች በስተቀር በትዳር አጋር ስለሚፈፀም ጥቃት አያንሱ፡፡ ተጎጂዋ የመጣችው ከሌላ ሴት ጋር እንኳ ቢሆን አብራት ያለችው አማትዋ፣ የወንድሟ ሚስት ወይም ዘመድ ልትሆን ትችላለች፡፡
- ስለጥቃት ጥያቄ የሚያቀርቡ ከሆነ አቀራረብዎ የሰውን ስሜት በተረዳና ከፍረጃ በፀዳ አኳኋን መሆን አለበት
- በሚሰሩበት ማህበረሰብና ባህል ዘንድ ተስማሚና ተገቢነት ያለው ቋንቋ ይጠቀሙ

**ተጎጂዋ የጥቃቱን ክስተት/ቶች ይፋ ካደረገች፡-**

- ህይወት አድን ድንገተኛ ህክምና፣ የአባለዘር በሽታ ህክምናና ያልታቀደ እርግዝናን መከላከያ አገልግሎቶች ለምሳሌ ድንገተኛ የእርግዝና መከላከያ ይስጧት
- ተጎጂዋ የተለያዩ አገልግሎቶችን ማግኘት እንድትችል ወደ ሌሎች አገልግሎቶች ሪፈር ያድርጓት
    - የቤት ውስጥ ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎች ወደ መጠጊያ ቤቶች/ማቆያዎች እንዲገቡ መንገዶችን ያመቻቹላቸው
- ህፃናት ወይም የስምምነት ፈቃድ መስጠት የማይችሉ አዋቂዎች በሚያጋጥሙበት ወቅት ተጎጂዎቹ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች የእርዳታ ፍለጋ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ያበረታቱ

**ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት መፈፀሙን ከተጠራጠሩና ነገር ግን ተጎጅው/ዋ ግልፅ ካላወጣ/ች፡-**

- አይጫኗት/ኑት፤ ይልቁንም ልትነግርዎ/ሊነግርዎ ስለምትፈልገው/ስለሚፈልገው ነገር እንድትወስን/እንዲወስን ጊዜ ይስጡት/ጧት
- ተጎጂዋ/ው አገልግሎቶችን ለመጠቀም ልትወስን/ሊወስን ስለምትችል/ስለሚችል ስለሚገኙት አገልግሎቶች ያብራሩለት/ላት
- ጥቃቱ በተጎጂዋ/ው ጤና ላይ ስለሚያስከትለው አሉታዊ ተፅእኖና በህጻናት ላይ ስለሚያደርሰው ጉዳት መረጃ ይስጡ
- ስለተከሰተው ነገር በግልፅ እንድታወራ/እንዲያወራ ተከታታይ የቤት ለቤት ጉብኝት ያካሂዱ

### ❖ በጤና ተቋማት ውስጥ የሚሰጡ የጤና ትምህርቶችን ማስተዋወቅ

ለጤና ባለሙያዎች በቂና ሁሉን አቀፍ ስልጠና በመስጠት ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን በተመለከተ ያላቸውን አመለካከት፣ እውቀትና ክህሎት ማሻሻል ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ በፋንታው እንደዚህ አይነት ጥቃቶችን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት በሚኖራቸው አስተዋፅኦ ላይ አዎንታዊ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡

በጤና ተቋማት ውስጥ የሚሰጡ የጤና ትምህርቶችን በሚከተሉት ተግባራት ማጠናከር ይቻላል፡

- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል በጤና ተቋማት ውስጥ የሚሰጡ የጤና ትምህርቶች ቋሚ አጀንዳ ማድረግ
- በጤና ተቋም ውስጥ ትምህርቱን የሚታደሙትን ሰዎች ውይይት እንዲያካሂዱና ያላቸውን ግንዛቤ እንዲፈትሹ ለማድረግ የሚከተሉትን ርእሰጉዳዮች ያንሱላቸው፡-
    - ስለስርዓተ-ፆታ ያላችሁ አመለካከት ምንድነው?
    - "ስርዓተ-ፆታዊ እኩልነት" ሲባል የሚሰጣችሁ ትርጉም ምንድነው?
    - ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ምንድነው?
    - በእንደዚህ አይነት ጥቃትና በስርዓተ-ፆታ መካከል ያለው ቁርኝት ምንድነው?

- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ስላደረገ ጥቃት/ስለወሲባዊ ጥቃት የሰማቻችሁት አፈታሪኮችና እውነተኛ ታሪኮች አሉ?
- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ወገኖች ለማገዝ መወሰድ የሚገባቸው የመጀመሪያ እርምጃዎች ምንድናቸው?
- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ከወሲባዊ ጥቃት ጋር በተገናኘ ስለሚሰጡ አገልግሎቶች ምን የምታውቁት ነገር አለ? ጠንካራ የሪፈራል ትስስር ለጥቃት ተጎጂዎች ጠቃሚ ነው ብላችሁ የምታስቡት ለምንድነው?

## የሞጁል 4 ማጠቃለያ

ይህ ሞጁል አጋላጭ ሁኔታዎችን በመለየትና በመቀነስ እንዲሁም ለጥቃት ተጎጂዎች በቂ ምላሽ በመስጠት ለሚከናወነው ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ቅድመ መከላከል ተግባር አፅንኦት ሰጥቷል፡፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ስነምህዳራዊ ማእቀፍ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን መጠን ለመረዳትና በመከላከል እስትራቴጂዎች ውስጥ ምን ያህል የተለያዩ ደረጃዎችና ምክንያቶች መስተናገድ እንዳለባቸው ማየት አስችሏል፡፡ አስቀድሞ መከላከል አክሞ ከማዳን የተሻለ ሲሆን በጤናው ሴክተር ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው በጥሩ አፈፃፀም የተከናወኑ ተግባራት ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን የመከላከል አስተዋፅኦ እንዳላቸው መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ የመከላከል እስትራቴጂዎች በማህበረሰብ ደረጃ እና በተቋም ደረጃ የሚካሄዱ ሲሆኑ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የመከላከል ተግባራትን በማስፈፀም ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ ሞጁል የጤና ባለሙያዎች የሚያከናውኑት ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎችን በጊዜ የመለየት ተግባር ለተጎጂዎቹ የተሻለ እንክብካቤ ለመስጠት አስተዋፅኦ እንዳለው አሳይቷል፡፡ ይህም ሆኖ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት በሚያስከትላቸው ተፅእኖዎች ሰፊው ማህበረሰብና የተጎጂ ቤተሰቦች እንደሚጎዱ ማወቅ አለብን፡፡ ስለሆነም የእነሱም ፍላጎቶች ሊስተናገዱ ይገባል፡፡

## የተሳታፊዎች ግለምዘና

- ምን ተማሩ?

- ምን አይነት እውቀቶችንና ክህሎቶችን ማሻሻል ቻሉ?

- መሻሻል ይቀረዋል የሚሉት እውቀትና ክህሎት ምንድነው?